PEPSICO

# PepsiCo, Inc. የአለም አቀፍ አቅራቢ የስነምግባር ደንብ

ተግባራዊ የሆነው ጁን 2018 ነው
አገስት 2025 የተሻሻለ

## ዓላማ እና የፍጻሜ ክልል

PepsiCo ውስጥ ያለን ሰዎች፣ በስነ-ምግባርና በኃላፊነት መንቀሳቀስ ትክክለኛው ብቻ ሳይሆን ለንግድ ስራችንም ማድረግ ያለብን ትክክለኛው ነገር ነው ብለን እናምናለን። ይህ እምነት በምናደርገው በማንኛውም ነገር ውስጥ የተሳሰረ ሲሆን እርሱ የራዕያችን መሰረት ነው፡- ከ pep+ (PepsiCo Positive) ጋር ሆኖ በማሸነፍ በተስማሚ ምግቦች እና መጠጦች ውስጥ አለም አቀፍ መሪ መሆን። የእኛ የአለም አቀፍ አቅራቢ የስነምግባር ደንብ (“**የአቅራቢ ደንብ**”) በንግድ ታማኝነት፣ በስነምግባር እና ፀረ-ሙስና፣ የሰብዓዊ መብቶች እና በስራ ደንቦች፣ በጤናና ደህንነት እንዲሁም በአካባቢ አያያዝ ውስጥ ያስቀመጥናቸውን አለም አቀፍ ደረጃዎች ያንጸባርቃል፣ እንዲሁም ለአቅራቢዎቻችን ያስቀመጥናቸውን ተጠባቂ ነገሮች ይዘረዝራል።

ሁሉም አቅራቢዎች፣ ሻጮች፣ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ኤጀንቶች እንዲሁም ሌሎች እቃዎችንና ግልጋሎቶችን የሚያቀርቡ ከPepsiCo (“አቅራቢዎች”) ወክለው ለንግድ የሚያቀርቡ ሶስተኛ ወገኖች በPepsiCo እና ቅርንጫፎቻቸው በተቀመጠው ሁኔታ መሰረት የአቅራቢ ደንብንና ሌሎች ተገቢ ፖሊሲዎችን[1] እንዲከተሉ ይጠበቅባቸዋል። አቅራቢዎች በአቅርቦት ሰነስለት ውስጥ የአቅራቢ ደንብ እና ተገቢ ፖሊሲዎችን መተግበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም፣ በPepsiCo ቦታዎች ላይ የመስክ አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ወይም የPepsiCo መገልገያ ወይም ንብረት የሚጠቀሙ አቅራቢዎች ከስራ ቦታ ባህርይ እና የመሳሪያ እና ንብረት አግባብ የሆነ አጠቃቀም ጋር የተገናኙ ሁሉም የPepsiCo መስፈርቶችን ማክበር አለበት።

## የንግድ ሥራ ባህሪይ መርሆዎች

PepsiCo አቅራቢዎቹ ንግድ ሲፈፅሙ ሀላፊነት በተሞላበት፣ በታማኝነት፣ በሀቀኝነትና በግልፅነት እንዲያደርጉ እንዲሁም የሚከተሉትን ስርዓቶችን እንዲያከብሩ ይጠብቃል፡-

1. **ግንዛቤ በማስጨበጥ እንዲሁም በሚሰሩባቸዉ ሀገራት የተቀመጡትን ህጎችና ደንቦች ማክበር።**

2. **የPepsiCo እና የአጋሮቻቸዉን መረጃ በሙሉ በሚስጥር መጠበቅ።**

   የ PepsiCo እና የአጋሮቻቸውን መረጃ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል በሚኖረዉ ፈቃድ፣ ለህጋዊ የንግድ ፍላጎት ተብሎ (ማለትም ማወቅ ለሚያስፈልገው ብቻ የሚጋራ መረጃ) እና በህጋዊ ስምምነት ላይ ተመስርቶ መረጃ ማሳየት በትክክል ከተፈቀደ ብቻ እንጂ በPepsiCo ውስጥም ሆነ ውጪ የPepsiCo አቅራቢዎች ለማንም ሰው መረጃ አለማሳየትን ጨምሮ ማንኛውም ተገቢ እና አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ጥንቃቄዎች መቀበል ይገባቸዋል።

3. **ለPepsiCo የንግድ እንቅስቃሴ በተገቢዉ መንገድ በመወዳደር ሁሉንም የንግድ ስራዎች በ PepsiCo ስም ህጋዊ በሆነ አካሄድ ማከናወን።**

   PepsiCo የንግድ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ህጋዊና ስርዓት በተሞላበት ለመፈፀም ቃል የገባ ሲሆን ከደንበኞች፣ ከአቅራቢዎች፣ ከመንግስት ሃላፊዎችና ሌሎች ሶስተኛ ክፍል ወገኖች ጋር የሚደረጉ የሙስና አሰራሮችን በጥብቅ ይከለክላል። እንዲሁም የPepsiCo አቅራቢዎች በማንኛዉም የንግድና የህዝብ ሴክተሮች ውስጥ በየትኛውም አይነት ሁኔታ የሙስና ድርጊት እንዳይፈፅሙ ይከለክላል። አቅራቢው በPepsiCo ስም በመጠቀም ቃል ገብቶ ሲሰራ፣ ለመንግስት አካላት ወይም ለማንኛውም ግለሰብ እንዲሁም የግል ወይም የንግድ ሴክተር አካል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዋጋ ያለውን ማንኛውም ነገር አቅርቦ ክፍያ በመፈፀም ተቀባዩ ስልጣኑን ያለአግባብ እንዲጠቀም ወይም ፍትሃዊ ያልሆነ የንግድ ግንኙነት ወይም የግል ጥቅም እንዲያገኝ ማድረግ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ አይፈቀድም። ከእነዚህ ስርዓቶች ጋር በመስማማት፡ አቅራቢዎች PepsiCoን በመወከል ሲሰሩ፡ ከዩኤስ የዉጪ ግንኙነት ፀረ ሙስና ደንቦችን፣ በአካባቢዉ ያሉ የፀረ ሙስና ህጎችን መስማማት፤ እንዲሁም የ PepsiCo አለም አቀፍ ፀረ-ጉቦኝነት እና ተገዥነት ፖሊሲን (“ABAC ፖሊሲ”) ማስከበር አለበት።

4. **ከማግለል፣ ከትንኮሳ ወይም ከሌሎች አይነት ጥቃቶች ነፃ የሆነ የስራ ቦታን መፍጠር።**

   የPepsiCo እቅራቢዎች፣ ሰራተኞችና የቢዝነስ አጋሮች ለሚያበረክቷቸው አስተዋጽኦዎች ዋጋና ክብር የሚሰጡበት የስራ አካባቢ መፍጠር ይኖርባቸዋል። ትንኮሳ፣ ማለትም ያልተፈቀደ በቃል፣ በምስል፣ በአካል ወይም በሌላ የትኛውም ዓይነት መልኩ የሚፈጸምና የሚገለጽ አስፈሪ፣ አስቀያሚ ወይም ምቹ ያልሆነ የስራ አካባቢ የሚፈጥር በትዕግስት አይታለፍም። የቅጥር ውሳኔዎች በብቃት፣ በሙያ፣ በአፈፃፀም ደረጃ እንዲሁም በስራ ልምድ ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው።

---

[1] የሚተገበሩ ደረጃዎች እና ፖሊሲዎች ከሚያካትቱት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡- የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግ፣ የዓለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት መሰረታዊ መርሆዎች እና የስራ መብቶች መግለጫ፣ የPepsiCo's ዓለም አቀፍ የጸረ-ጉቦኝነት ተገዥነት ፖሊሲ፣ እናየPepsiCo ዘላቂ የፓልም ዘይት ላይ ያለ ዓለም አቀፍ ፖሊሲናቸው። የእነዚህ ሰነዶች እና ሌሎች ጠቃሚ የሆኑ የPepsiCo ፖሊሲ ቅጂዎች በwww.pepsico.comላይ ሊገኙ ይችላሉ።

**5. ሰራተኞችን በአግባቡ መያዝ ያስፈልጋል ይህም ደሞዝን፣ የስራ ሰዓትንና ጥቅማጥቅሞችን ያጠቃልላል።**

የ PepsiCo አቅራቢዎች ሁሉንም ተገቢ የደሞዝ ክፍያዎች፣ የስራ ሰአታት፣ እንዲሁም የጥቅም ህጎችና የደንብ ፍላጎቶችን ማክበር አለባቸው። አቅራቢዎች ዝቅተኛ የሆነ ህጋዊ ደረጃን የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደሞዞችን ማቅረብ አለባቸው እና በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃን ለመሸፈን የሚበቃ ደሞዝ ለማቅረብ መትጋት አለባቸው። ሁሉም ደሞዞች በጊዜው እና በሙሉ ክፍያ መከፈል አለባቸው እና የደሞዝ መቁረጥን እንደ ስነምግባር እርምጃ አድርጎ መውሰድ የተከለከለ ነው። አቅራቢዎች የአለም አቀፍ የስራ ሰአትና የእረፍት ቀናት ደረጃዎችን ለማስከበር መጣር ይኖርባቸዋል፦ እነዚህም የሚያጠቃልሉት (i) ከ 48 ሰአት ያልበለጠ በመደበኛነት የተቀመጠ የስራ ሰአት እንዲሁም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ 12 ተጨማሪ ሰዓታት እና (ii) ተጨማሪ ሰዓት ከፍ ያለ ክፍያ በመክፈል መካስ (iii) በአደጋ ወይም ሌሎች ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ካልተከሰቱ በስተቀር ሰራተኞች በየ 7 ቀኑ አንድ ቀን እረፍት ያገኛሉ። የአቅራቢው ልምድ እነዚህን አለም አቀፍ ደረጃዎች ካላሟላ አቅራቢዉ መሰረታዊ የሆነውን ችግር ለይቶ አሰራሩን ማሻሻል አለበት።

**6. በሀይልም ይሁን በግዳጅ የሚደረግ ማንኛዉም አይነት የጉልበት ስራ መከልከል።**

PepsiCo ሁሉም አይነት የጉልበት ብዝበዛን ይከለክላል፣ ይህም የሚያካትተው ያለፈቃድ የሚደረግ የእስር ቤት ጉልበት ስራ፣ የታሰረ የጉልበት ስራ፣ የተያያዘ የጉልበት ስራ፣ የወታደር የጉልበት ስራ፣ የባርነት አያያዝ የጉልበት ስራ እና ማንኛዉም ህገወጥ የሰው ዝውውር ነው። የ PepsiCo አቅራቢዎች የሰራተኞችን የመንቀሳቀስ መብትን ጨምሮ እነዚህን ደረጃዎች እና መሰረታዊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶችን ማክበር አለባቸው። የቅጥር አፈፃፀሞች ነፃ በሆነ ምርጫ የሚደረግ ሲሆን ለመቅጣት ወይም ለመቆጣጠር ተብሎ የሚደረግ በግዳጅ ወይም ከፈቃድ ውጪ የሆነ በእስር የሆነ የጉልበት ስራ፣ አካላዊ ቅጣትና ማስፈራራት ወይም ሌላ አይነት አካላዊ፣ ጾታዊ፣ ስነልቦናዊ ወይም መጥፎ ንግግሮች ሊኖር አይችልም። የቅጥር ውሎች (ለምሳሌ፣ የስራ አቅርቦት ደብዳቤ፣ ወዘተ.) የቅጥር ሁኔታዎችን በግልጽ መጥቀስ አለባቸው እና ሰራተኛው በሚገባው ቋንቋ አስፈላጊ ሲሆን በቃል ገለጻን በማቅረብ መሆን አለበት። አቅራቢዎች የሰራኞችን ወደሌላ ቦታ የመሄድ መብት ለመከላከል ሲባል የመታወቂያ ወረቀቶችን መያዝ፣ ተቀማጭ ገንዘብ መያዝ ወይም ሰራተኛዉ ስራውን እንዲያቋርጥ የማያስችሉ ሁኔታዎችን ማስቀመጥ የለባቸውም። ከአሰሪ የሚከፍልበት መርህ ጋር አብሮ በመሄድ፣ ሰራተኞች የስራ ቅጥራቸውን ለማግኘት ወይም ለማቆየት የቅጥር ወይም ሌላ ተመሳሳይ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ መጠየቅ የለበትም። የቅጥሩ ወጪ በአሰሪው መሸፈን አለበት። አቅራቢዎች እና የሶስተኛ ወገን የቅጥር ኤጀንሲዎች እነዚህን መርሆዎች ያከብራሉ እና በተቻለ ቦታ ሁሉ ያሉትን ክፍያዎች ለማካካስ ምክንያታዊ የመፍትሔ እቅድ ያወጣሉ።

**7. የልጆችን የጉልበት ብዝበዛ መከልከል።**

PepsiCo ከ (15) አመት በታች የሆኑ ግለሰቦችን፣ በአካባቢው ያለዉ ዝቅተኛ የሆነው የስራ እድሜ ክልል ወይም የትምህርት የመጀመሪያ እድሜ ከሆኑት ማለትም ከእነዚህ መካከል ትልቁ እድሜ ከሚሆነዉ በታች መቅጠር ይከለክላል። የPepsiCo አቅራቢዎች ለእነዚህ ደረጃዎች፣ ሁሉም የሚመለከታቸው ህጎች እና ደንቦች እንዲሁም ሁሉም ጠቃሚ የዓለም የስራ ድርጅት (ILO) ደረጃዎችን ይከተላሉ። ከILO መመሪያ ጋር አብሮ በመሄድ፣ በምንም ሁኔታ አንድ አቅራቢ ታዳጊ የሆኑ ሰራተኞችን ለጤናቸው እና ደህንነታቸው አደገኛ ሊሆን የሚችል ስራን እንዲያከናውኑ አይፈቅድም። በቅጥር ሰዓት አቅራቢዎች የሁሉንም ሰራተኞች እድሜ እና የቅጥር ብቁነት ማረጋገጥ አለባቸው፣ እና ማናቸውም ሊሆኑ የሚችሉ የፖሊሲ ጥሰቶችን በምክንያታዊነት ለመቀነስ አግባብነት ያላቸው ስርዓቶችን መመስረት አለባቸው። በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ የPepsiCo አቅራቢዎች የ United States Department of Homeland Security’s E-Verify ፕሮግራምን በመጠቀም የቅጥር ብቁነትን ያረጋግጣሉ፤ እንዲሁም በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም የእነርሱ የሰራተኛ ኤጀንሲዎች፣ ንኡስ ስራ ተቋራጮች እና አቅራቢዎች E-Verify ጥቅም ላይ እንዲውል ያስገድዳሉ።

**8. ሰራተኞች በማህበር የመደራጀትና በሕብረት የመደራደር መብት እንዳላቸው እውቅና መስጠት።**

ከህጉ ጋር በተጣጣመ መልኩ የ PepsiCo አቅራቢዎች የሰራተኞቻቸውን በማህበር ውስጥና በሰራተኞች ማህበር ዉስጥ የመሳተፍ መብቶችቻቸውን ሊያከብሩ ይገባል። የዩኒየን አባላት፣ የሰራተኛ ማህበር ተወካዮች እና ወደ እነዚህ ድርጅቶች ለመቀላቀል ወይም ለመቆጠብ እነዚህን መብቶች ለመተግበር የሚፈልግ ማንኛውም ሰራተኛ ላይ የሚደረግ ማስፈራሪያ፣ ትንኮሳ፣ ብቀላ ወይም ማወክ መፈጸም ክልክል ነው። በማህበር የመደራጀት ነጻነት በአካባቢያዊ ህግ በሚገደብበት ወቅት፣ አቅራቢዎች የአካባቢ ህግን አክብረው አማራጭ ተሳትፎን ለመደገፍ መትጋት አለባቸው።

**9. ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የስራ ሁኔታ ማዘጋጀት።**

የ PepsiCo አቅራቢዎች የጤናና የደህንነት አደጋዎችን በንቃት በመከታተል በስራ ቦታ የሚደርሱትን ጉዳቶችና ህመሞችን የመከላከል ስራዎችን መስራት አለባቸው። አቅራቢዎች ከተወሰነ ኢንዱስትሪ ጋር የተያያዙ አደገኛ ነገሮችን የሚለዩ፣ አደጋዎችን የሚመዝኑ እና የሚቆጣጠሩ የአስተዳደር ስርዓቶች እና መቆጣጠሪያዎችን መተግበር እንዲሁም የጤና እና የደህንነት አደጋዎችን በንቃት ለመሸፈን ስልጠና ማቅረብ እንዲሁም የጤና እና የደህንነት አፈጻጸማቸው ተከታታይ መሻሻል ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪም አቅራቢዎች የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ የንፅህናና የጤና ማለትም በቂ የሆነ እረፍት ማድረጊያ ክፍልና የእጅ መታጠቢያ መርጃዎች፣ የእሳት አደጋ መውጫ በሮች እንዲሁም አስፈላጊ የእሳት ማጥፊያ፣ የግል መጠበቂያ መሳሪያ [Personal Protective Equipment (PPE)] የድንገተኛ አደጋ መርጃ መሳሪያዎች እና በአደጋ ጊዜ የሚካተቱ አካባቢያዊ፣ የእሳትና የጤና ምላሽ መስጫ አገልግሎቶችን ማቅረብ አለባቸዉ።

**10. ለሁሉም የሚመለከታቸው አካባቢያዊ ህጎች እና ደንቦች መገዛት እንዲሁም አካባቢያዊ ተጽዕኖዎችን የሚያንሱባቸውን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎች ማከናወን።**

የPepsiCo አቅራቢዎች በጊዜ ሂደት ሁሉንም የሚመለከታቸው ህጎች ማክበር እና የንግድ ሥራ ክንውኖቻቸው የአካባቢያዊ ተጽእኖን በወጥነት ለመቀነስ መጣር አለባቸው። በውሃ እና የኃይል አጠቃቀም የውጤታማነት መሻሻያዎች፣ የውጋጅ ቅነሳ፣ የቁሳቁስ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እና የብክለት መቆጣጠሪያ ማሻሻያዎች በኩል የተፈጥሮ ሃብቶች የአያያዝ እድሎች ለንግድ ሥራ ክንውኖች ወሳኝ መሆን አለባቸው። የውሃ አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማሻሻል፣ ውጋጅን ለመቀነስ እና ወደ ቆሻሻ መጣያ የሚላከውን ውጋጅ ለማስወገድ እና የብዝሃ ህይወት አያያዝን ወደ ምንጭ እና ክንውኖች ለማዋሃድ የእርምጃ እቅዶችን ለማከናወን PepsiCo አቅራቢዎቹን ያበረታታል።

**11. ከሚመለከታቸዉ የህግና የደንብ ፍላጎቶች ጋር የተጣጣመ የሂሳብ መዝገቦችና የንግድ አያያዞች በመተግበር እንዲሁም ወደ PepsiCo የሚገቡ ሁሉም አይነት ክፍያዎችና ተመላሽ ሂሳቦችን ጨምሮ ተቀባይነት ባላቸዉ የሂሳብ አያያዝ መንገዶች መቀበል።**

**12. ተቀባይነት ያላቸዉ ጥራትና ደህንነታቸዉ የተጠበቁ የምግብ ደረጃዎችን ያሟሉ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ማቅረብ።**

PepsiCo በሁሉም ኩባንያዎቻችን ላይ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን እና ደህንነታቸው የተጠበቁ ምርቶች ለማምረት ቁርጠኞች ነን። ምርቶቻችንን በማምረት፣ በማንቀሳቀስ፣ በማሸግ ወይም በማከማቸት ተግባር ውስጥ በማንኛውም መልኩ ተሳታፊ የሆኑ አቅራቢዎች፡ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅብዎታል፡-

- እርስዎ ባሉበት ቦታ የሚመረቱ ምርቶችን የሚመለከቱ የምርት ጥራት ደረጃዎች፣ ፖሊሲዎችና አሰራሮችን ማወቅ እና መተግበር፤
- መልካም የአመራረት አሰራሮችንና የፍተሻ ፕሮቶኮሎችን መከተል፤
- አግባብነት ያላቸውን በፌደራል፣ በስቴት፣ እና በአከባቢ መንደር ደረጃ ያሉት የምግብ ደህንነት ሕጎችና ደንቦች በሙሉ መከተል፤ እና
- የ PepsiCo ምርት ጥራትና በህብረተሰቡ ዘንድ ያለዉን ጎን ሊጎዳ የሚችል ሁኔታ ሲፈጠር ለ PepsiCo ሪፖርት ማድረግ።

**13. የአቅራቢዉን አሰራር ድጋፍ በማድረግ አግባብነት ያለዉ የአስተዳደር ሂደት መመስረትና በ PepsiCo ጥያቄ መሰረት በምክንያት የተደገፈ ግምገማ ማድረግ።**

ከ PepsiCo ጋር አብሮ ቢዝነስ ለመስራት አቅራቢዎች የአቅራቢነት ደንብን እንዲያከብር በሚያስገድደዉ ዉል እና የግዥ ትእዛዝ ማስፈጸሚያ ውስጥ ይገባሉ። በአቅራቢ ኮድ ውስጥ የተዘረዘሩ ደረጃዎች እና የሚጠበቁ ነገሮች ጋር ቀጣይ ተገዥነትን ለመደገፍ አቅራቢዎች አግባብነት ያላቸው ፖሊሲዎች፣ አሰራሮች እና የአስተዳደር ስርዓቶችን እንደሚከተሉ እንጠብቃለን። ቅድመ ማሳሰቢያ በማድረግ፣ PepsiCo አቅራቢዉን በአቅራቢ ስምምነት መሰረት እያከበረ እንደሆነ ለማረጋገጥ የሰብዓዊ መብቶች ኦዲቶች እና ሌላ ኢላማ የተደረጉ ምዘናዎችን ጨምሮ ምክንያታዊ ኦዲቶችን ለማከናወን ሊጠይቁ ይችላሉ። በተጨማሪም ከአቅራቢ ኮድ ጋር ተገዢነትን ለማሳየት ስልጠናዎችን ለማጠናቀቅ PepsiCo አቅራቢዎችን ሊጠይቅ ይችላል። በየተባበሩት መንግስታት የቢዝነስ እና የሰብዓዊ መብቶች የመመሪያ መርሆዎች እንደተገለጸው አቅራቢዎች የራሳቸውን የሰብዓዊ መብቶች ተገቢ ጥንቃቄ እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪ በ ABAC ፖሊሲ በዝርዝር እንደተቀመጠው፣ አንዳንድ አቅራቢዎች የእኛን የስስተኛ ወገን የመቻቻል ሂደት ከጊዜ ወደ ጊዜ ማጠናቀቃቸውን ይጠይቃል።

**14. ከPepsiCo ሰራተኞች ጋር ሲገናኙ ሊፈጠሩ የሚችሉ የፍላጎት ጥሰቶችን ያስወግዱ።**

የ PepsiCo አቅራቢዎች ለ PepsiCo ሰራተኞች የ PepsiCoን የቢዝነስ ዉሳኔ ወይም ጥቅም ትክክል ባልሆነ መልኩ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ተፅእኖ በማሳደር ስጦታዎችን ማቅረብም ሆነ መስጠት የተከለከለ ነው። አቅራቢዎች አንዳንድ ጊዜ የሚደረጉ ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ተገቢ ስጦታዎች (ከ$100 የአሜሪካ ዶላር በታች ዋጋ ያላቸው) ብቻ በሚፈቅዱ እና (1) በውል ስምምነቶች ወይም በጨረታ ሂደት ወቅት እና (2) በግዢ ሚናዎች ውስጥ ላሉ ሰራተኞች የሚደረጉ ማናቸውም ስጦታዎችን የሚከለክሉ የPepsiCo የንግድ ስጦታ ገደቦች ስር ይገዛሉ። አቅራቢው ከPepsiCo ሰራተኞች ጋር ሲገናኝ የጥቅም ግጭቶችን ሊያመጣ የሚችሉ ወይም የጥቅም ግጭትን የሚያመጡ የሚመስሉ ማናቸውም ሌላ እንቅስቃሴዎችን ያስወግዳል።

**15. ሁሉም የመሬት ይዞታዎች (መከራየት እና መጠቀም የሚያጠቃልል) ቀዳሚና የታወቁ ስምምነቶችን ጨምሮ የአለም አቀፉን የፋይናንስ ኮርፖሬሽን (IFC) የብቃት ደረጃዎች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ።**

**16. የቅሬታ አያያዝ ሂደቶችን መመስረት እና የአቅራቢ ኮድ የተጠረጠሩ ጥሰቶችን ሪፖርት ማድረግ።**

አቅራቢዎች ሰራተኞች በክንውናቸው ውስጥ እና በሶስተኛ ወገን አካላት የሚነሱ ቅሬታዎችን ወደበላይ አካል ለማስተላለፍ፣ ለማስተዳደር እና ለመፍታት የቅሬታ አስተዳደር ዘዴን መመስረት አለባቸው። የዘዴ መዋቅር እና ተግባራት በንግድ እና የሰብዓዊ መብቶች ላይ የተባበሩት መንግስታት የመመሪያ መርሆዎች ውስጥ ከተዘረዘሩ የመስፈርቶች ውጤታማነት ጋር አብረው መሄድ አለባቸው። አቅራቢዎች ስጋቶችን በቅን ልቦና የሚያነሱ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ላይ የበቀል እርምጃ እንዳይወሰድ በግልጽ መከልከል አለባቸው። የበቀል እርምጃ የሚያካትተው ነገር ግን በዚህ ብቻ የማይወሰን በቅን ልቦና ስጋት እንዳለ ባነሳ ግለሰብ ወይም ድርጅት ላይ ማንኛውም ህጋዊ እርምጃ፣ የኢኮኖሚ የበቀላ እርምጃ፣ ሆን ተብሎ የስም ማጥፋት ጉዳት፣ ዛቻዎች፣ ማስፈራራት እና ጥቃት ማድረስ።

PEPSICO

አቅራቢዎች እና የእነርሱ ሰራተኞች የዚህ ደንብ ጥሰቶች ጥርጣሬዎችን በ PepsiCo “Speak Up” መስመር በዩናይትድ ስቴትስ 1-866-729-4888 ወይም በሌሎች የአለም ክፍሎች በሚገኙ ሀገሮች በሙሉ በተዘጋጀው ስልክ መስመር ሊያሳውቁ ይችላሉ። አለም አቀፍ የስልክ መስመር ቁጥሮች ዝርዝር እዚህ ጋር ይገኛል። “Speak Up” መስመር በአለም አቀፍ ደረጃ ለ 24/7 ሰአት ክፍት ነዉ፡፡ ተግባቦቶች በ“Speak Up” የድር መስመር አድራሻ ላይ በኤሌክትሮኒክ መንገድ እንዲሁ ሊከናወን ይችላል (እዚህ ጋር ይመልከቱ)። እነዚህ ሁሉ ሪፖርቶች በ Speak Up ነክ መስመርም ይሁን በድረ ገፅ መስመር ቢቀርቡ ሚስጥራዊ እንደሆኑ ይቆያሉ እንዲሁም በህግ በተፈቀደዉ መሰረት ማንነትዎ አይገለፅም።